# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# ሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

## ለጤና ተሰማሚ መኖርያ ቤት አሰራርና አያያዝ ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1
2. አጠቃላይ ዓላማ ........ 2
3. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 2
4. ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ በሚመለከትየሚከናወኑ ተግባራት ........ 11
4.1. በቤተሰብ ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃ ማሰባሰብ፤ ........ 11
4.2. ህብረተሰቡን ያሳተፈ የሥራ እቅድ ማውጣት ........ 11
**4.3 ከ1 ለ5 ትስስር እና የሴቶች ልማት ቡድን ጋራ መስራት** ........ 12
4.4 ለፓኬጁ ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉ ማህበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ከአጋሮች ጋር አብሮ መስራት ........ 12
4.5 ህብረተሰቡን በመቀስቀስ በማስተማር፣ በማስተባበር፣ ተሳትፎውን በማሳደግ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ፤ ........ 13
4.6 አዲስ መኖሪያ ቤቶችን በተሻሻለው የአሰራር ዘዴ እነዲሰሩ ማድረግ ........ 13
4.7 የነባር መኖሪያ ቤቶችን ማሻሻል ........ 13
4.8 በሰርቶ ማሳያ በማዘጋጀት ህብረተሰቡ የተሻለ ክህሎት ማስጨበጥ ........ 15
4.9 ምርጥ ተሞክሮ መለየት፣ መቀመርና ማስፋት ........ 16
4.10 የማበረታቻ ዘዴዎች በመጠቀም በጎ ተሞክሮ ያላቸውን ሰዎች ማበረታታት ........ 16
4.11 አካባቢያዊና ሕጋዊ ደንቦችን መጠቀም፣ ........ 16
4.12 የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ማካሄድ፣ ........ 16
5. የጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤቶችን አሰራር ለማስተማርና ለማስረጽ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ........ 17
6. ከጤና ጣቢያ ጋር አብሮ መስራት ........ 18
7. ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት አሰራርና አያያዝ በአግባቡ በመተግበር የሚጠበቁ ውጤቶች ........ 18
8. ክትትልና ግምገማ ........ 18
9. የፓኬጁ ጠቋሚዎች /indicators/ ........ 18

# 1. መግቢያ

መኖሪያ ቤት ለሰዎች አካላዊ ፣ኢኮኖሚያዊ፣ማኀበራዊና ሥነአእምሮአዊ ጤንነትንና ደኀንነትን ለመጠበቅ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ነው ።በመሆኑም ሰዎች አብዛኛውን የህይወት ዘመናቸውን የሚያሳልፉ ትበቤት ውስጥ ስለሆነ አንድ መኖሪያ ቤት ሊያሟላው የሚገባውን መስፈርት ያላሟላና ንጽህናው የተጓደ ለከሆነ በጤና ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይሆንም።

ለጤና ተስማሚ ያልሆነ መኖሪያ ቤት ሰዎችን ለቅዝቃዜ፣ላልተፈለገ ሙቀት፣ለተለያዩ አደጋዎች፣ለከፍተኛ ድምፅ፣ለቲቢ፣እንፍሎዌንዛ ግርሻ ተስቦና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች መሰራጨት እንዲሁም ለሥነ አእምሮአዊና ማኀበራዊ ቀውስ መፈጠር ዋነኛ ምክንያት ነዉ ። ለዚህ ዓይነቱ አስከፊ ሁኔታ የሚጋጡት በአብዛኛው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ቢሆኑ ምግንባር ቀደም ተጠቂዎች ግን ህጻናት፣ሴቶችና አረጋዊያንናቸው፡ ፡

በሀገራችን ያሉት የገጠር ቤቶች አብዛኞቹ ከቦታ መረጣና የቤቱአሰራር ለጤና ተስማሚ ካለመሆኑ ባሻገር የክፍሉም ብዛት አንድ ብቻ ሆኖ አገልግሎቱም ለከብቶች ማሳደሪያ፣ለዕቃ ማስቀመጫ፣ለምግብ ማብሰያና መመገቢያ፣ለእንግዳ መቀበያና ለመላው ቤተሰቡ መሰብሰቢያ ይውላል።በተጨማሪምተባዮች፣ቆርጣሚእንስሳት፣ለምሳሌትንኝ፣ዝንብ፣በረሮ/፣ተባዮች /ቅማል፣ ቁንጫ፣ትኋን፣ሙጃሌ/፣ቆርጣሚእንሰሳት/አይጥ፣አይጠመጎጥ/ እናተናዳፊነፍሳት /ጊንጥ፣እባብ፣ ናዝራ/ የመሳሰሉት በመኖሪያ ቤት አከባቢ በብዛት የሚኖሩ ከሆነ ተላላፊ በሽታዎች ከሰው ወደ ሰው ከእንስሳት ወደ ሰው በቀላሉይ ተላለፋሉ።በተለይም ከአይጦች፣ከውሾችና ከሌሎች የቤት እንስሳት በሽታዎች ወደ ሰው በቀላሉ እንዲዛመቱ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራሉ።በመሆኑም አንድ መኖሪያ ቤት ከነዚህ ተባዮችና ቆርጣሚ እንስሳት የጸዳ መሆን ይኖርበታል።

እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ለሰዎች መኖሪያነት የሚያገለግል ቤት ተገልጋዩን ከሙቀት፣ ከቅዝቃዜ፣ ከከፍተኛ ድምፅና አቧራ እንዲሁም ከበሽታ አምጪ ተዋህሲያን ለመከላከል የሚያስችሉ በቂ የውሃ አቅርቦት ፣የመፀዳጃ አገልግሎት፣የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያለው እንደ ቤተሰቡ ብዛት በቂ ክፍሎች ያሉትና በቂ የአየር ዝውውርና የፀሃይ ብርሃን ማስገባት የሚችል እንዲሁም የቤቱ አሠራር ከተለያዩ አደጋዎች ለመከላከል የሚያስችል እና በሽታ አስተላላፊ ለሆኑ በራሪ ነፍሳትና ቆርጣሚ እንሰሳት መራቢያነትአመቺያልሆነመሆንይኖርበታል፡ ፡

ስለሆነም ከመኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ ያለውን የጤናና የደህንነት ችግር ለማስወገድ ሕብረተሰቡን ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንዲቻል ይህ ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ፓኬጅ ተዘጋጅቷል።

## 2. አጠቃላይ ዓላማ

- ሕብረተሰቡ ለጤና ተስማሚ የሆነ የመኖሪያ ቤት እንዲኖረው በማድረግ እራሱንና ቤተሰቡን ከተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችና አደጋዎች መከላከል፡፡

## 3. ዝርዝር ዓላማዎች

- ሕብረተሰቡ በመኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ጉድለት እንዲሁም በተባዮች፣በቆርጣሚ እንስሳት፣ በበራሪና ተናዳፊ ነፍሳት ሊከሰቱ ከሚችሉ የጤና ችግሮች በቂ ግንዛቤና ዕውቀት በማዳበር የአመለከከት ለውጥ እዲያመጡ ማድረግ፡፡
- ሕብረተሰቡ ለመኖሪያ ፣ለምግብ ማብሰያ፣ ለመኝታና ለመመገቢያ ወዘተ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ክፍሎችን ሠርቶ እንዲጠቀም ለማድረግ፣
- ሕብረተሰቡ አዳዲስ መኖሪያ ቤቶች ሲሰራም ሆነ ነባር ቤቶችን ሲያሻሽል ለጤና ተስማሚ የመኖሪያ ቤት ንድፍ የመጠቀም ልምዱ እንዲዳብር ለማድረግ፡
- ሕብረተሰቡ በቤት ውስጥ በሚፈጠር የአየር ብክለት ምክንያት የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን እና መከላከያ ዘዴዎችን ተረድቶ አንዲከላከል ማድረግ፡፡

**ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት**

የአለምጤናጥበቃድርጅትለጤናተስማሚመኖሪያአካባቢብሎባወጣውየመመዘኛነጥቦችመሰረት የመኖሪያ አካባቢ፣

- ❖ ነዋሪዎቹንከሙቀት፣ከቅዝቃዜ፣ከከፍተኛድምፅናአቧራከመሳሰሉትለመከላከልየሚያስችል፣
- ❖ በቂናለጤናተስማሚየሆነየውሃአቅርቦትያለው፣
- ❖ በቂየመፀዳጃአገልግሎት፣የደረቅና፣ፍሳሽቆሻሻማስወገጃዝግጅትያለው፣
- ❖ የቤቱአሰራርከተለያዩአደጋዎችለመከላከልየሚያስችል፣
- ❖ አንደቤተሰቡብዛትበቂክፍሎችያሉትናበቂየአየርዝውውርናየፀሐይብርሃንማስገባትየሚችል፣
- ❖ በማገዶጭስምክንያትሊከሰቱየሚችሉትንየቤትውስጥአየርብክለትለመከላከልየሚያስችል፣
- ❖ ለቤተሰቡአገልግሎትየሚውለውምግብከአያያዝናአቀማመጥጉድለትየተነሳእንዳይበላሽበቂየሆነንፅህናውየተሟላማ ስቀመጫያለው፣
- ❖ በሽታ ተአስተላላፊ ከሆኑበራሪነፍሳትናቆርጣሚአንስሳትአንዲሁም ከመጥፎ ሽተነፃ የሆነና፣
- ❖ በአካባቢው መዝናኛ ቦታና ለማህበራዊ አገልግሎት ቅርበት ያለው ቢሆን ይመረጣል፡፡

**የመኖሪያ ቤትና የአካባቢውን ንጽሕና አጠባበቅ**

- ❖ ቤትን በየጊዜው ማጽዳት፣ ወለልን መጥረግ፣ የወለል ምንጣፍ ካለ በሳምንት አንድ ጊዜ እያወጡ ማጽዳት፣
- ❖ የቤት ግድግዳዎችን ማጽዳት፣ መለሰን፣
- ❖ በግድግዳዎችም ሆነ በወለል ላይ የሚተዩ ስንጥቆችና ጉድጓዶች ለተባዮች፣ ለበራሪ ነፍሳትና አይጦች መደበቂያ እንዳይሆኑ መድፈን፣
- ❖ የቤቱን ውስጣዊና ውጭአዊ አካባቢ ከማንኛውም ዓይነት ቆሻሻና ከትርፍራፊ ምግብ የጸዳ ማድረግ፣
- ❖ አልጋ ከወለል በላይ ክፍተተ እንዲኖረው ሆኖ የመኝተታ ልብሶችንም አዘውትሮ ከቤት እያወጡ ፀሐይ ላይ ማስጣት፣
- ❖ የመኖሪያ ቤት ንጽህና ሊያጓድሉ የሚችሉ ለማዳ እንሰሳት ወደ ቤት አንዳይገቡ ማድረግ፣
- ❖ ምግብ የሚዘጋጅበትን ክፍል፣ የምግብ አዘገጃጀት፣ አቀማመጥና አያያዝ ንጽህናው እንዲጠበቅ ማድረግ፣
- ❖ ደረቅ ቆሻሻን ሰብስቦ በማቃጠል ወይም በመቅበር ማስወገድ፣
- ❖ ማንኛውንም የቤት ውስጥ እአጣቢና ፈሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ፣
- ❖ በራሪ ነፍሳትንና ቆርጣሚ አንስሳትን /ዝንቦች፣ሸረሪቶች፣ በረሮች፣ አይጦች፣ ወፎች ወዘተ/ ለማስወገድ መኖሪያ ቤቶችን በኘላን መሥራትና ዘወትር ቤትንና አካባቢውን ማጽዳት ያስፈልጋል፡፡

## ባለ ጭስ ማውጫ የምግብ ማብሰያ ምድጃ አሠራር

- ❖ በቤት ዉስጥ የሚከሰተዉን የአየር ብክለት ለመቀነስ ባህላዊ ጭስ አልባ ምድጃን እንዲጠቀሙ በማድረግ ተያያዥነት ያላቸዉን የጤና ችግሮች ለመከላከል፤
- ❖ ምድጃው ምግብ በምናበስል ጊዜ በግልጽ እንዲታይን በተቻለ መጠን መስኮት አጠገብ የሆነ ቦታ መምረጥ፣
- ❖ የምድጃው መጠን አራት ክንድ ስፋት፣ አንድ ሜትር ሁለት ክንድ ቁመት መሆን አለበት፣ ይህ መጠን ለመካከለኛ ምድጃ ሲሆን እንደባለቤቱ ፍላጐትና እንደቤቱ ስፋት የተሰጠው የስፋት መጠን ሊጨምር ይችላል፣
- ❖ ከፊት ለፊት ለእንጨት ወይም ለሌላ እቃ ማስቀመጫ እንዲያገለግል ክፍት ማድረግ፣
- ❖ በስዕሉ ላይ እንደሚታየው የጭቃውን ጡብ በሦስቱም በኩል እስከ ግድግዳው ድረስ በተቦካ ጭቃ አያይዞ ወደ ላይ መገንባት፣
- ❖ ወለሉና ግድግዳዉ  በጭቃ መለሰን፣
- ❖ በሚጣድበት እቃ ልክ ለክቶ ከፋፍሎ መገንባት፣
- ❖ የጭስ ማውጫውንም ቀዳዳ አብሮ ማያያዝና ቀዳዳዎቹ ውስጥ ለውስጥ በአንድ ወገን ብቻ እንዲገናኙ ማድረግ፣
- ❖ የጭስ ማውጫውን ቀዳዳ በደንብ ገንብቶ ከቤቱ ግድግዳ መካከል ወደ ውጭ እንዲወጣ ማድረግ፣
- ❖ ዙሪያውን በተቦካ ጭቃ መለሰን ቀዳዳ እንዳይኖረው መጠንቀቅ፣
- ❖ ከጐኑ ወይንም ከዳር በኩል ለሊጥ ማቡኪያና ለማሰሻ ማስቀመጫ ቦታ መተው፣ በደንብ ከደረቀ በኋላ ላስፈላጊው ግልጋሎት ማጠቀም፣





**ተባዮች**

ተባዮች አብዛኛውን ጊዜ ደም በመምጠጥ የሚኖሩ ነፍሳት ናቸው፡፡ በሽታን በማስተላለፍም በጣም የታወቁ ናቸው፡፡ በሽታን ከሰው ወደ ሰው ብቻ ሳይሆን ከእንስሳትም ወደ ሰው ያስተላልፋሉ፡፡ ከነዚህም ቅማል፣ ቁንጫ፣ ትኋን፣ ቅማንቿር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**ቅማልና ቅማንቿር**

የቅማልና የቅማንቿር ተፈጥሮና ልማድ ተመሳሳይ ስለሆነ ቅማል በማለት እናጠቃልለዋለን፡፡ ሆኖም ቅማንቿር የምትገኘው በብብት አካባቢና በሌሎችም መገጣጠሚያዎችና ደባቃ የሰውነት ክፍሎች ውስጥ ነው፡፡ በፅዳት የማይጠበቁ የሰውነት ክፍሎች፣ ፀጉር፣ የቆሸሸ ልብስ ለቅማል መራቢያና መኖሪያ ምቹ ነው፡፡ ቅማል የምትመገበው ደም በመምጠጥ ነው፡፡

**ቅማልና ቅማንቿር የሚያመጡት የጤና ችግሮች፡-**

- የደም ተስቦ /ታይፈስ/
- የግርሻ ትኩሳት /ሪላፕሲንግ ፊቨር/

**ማስተላለፊያ መንገድ**

የተስቦ በሽታና የግርሻ ትኩሳት አምጪ ረቂቅ ተዋህስያኑ በቅማሉ ሰውነት ውስጥ ስለሚገኝ በቅማሉ የተነከሰው የሰውነት ክፍል በማከክ በሚፈጠረው ቀዳዳ ወይም ቁስል የቅማሉ ዓይነ ምድር ሲገባ ወይም ቅማሉ ሲጨፈለቅ በሽታው ይተላለፋል፡፡

**መከላከያ ዘዴዎች**

- ሰውነትን ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በንፁህ ውሃና ሳሙና መታጠብ፣
- ፀጉርን በንፅህና መያዝ፣ ማበጠር፣ ማሳጠር፣ መላጨት፣
- የብብትና የመሳሰሉ ሰዋራ የሰውነት ክፍሎች በየጊዜው ማፅዳት፣
- የቀንና የሌሊት ልብሶች መለየት፣
- ልብስን በየጊዜው ማጠብና ቢቻል መተኮስ፣
- የሌሊት ልብስ ፀሐይ ላይ ማስጣት፣
- ቅማል ያፈሩ ልብሶችን በፈላ ውሃ መቀቀልና ፀሐይ ላይ ማስጣት፣
- ቅማልን በሰውነት ላይ ወይም በጣት አለመግደል፣
- ወረርሽኝ ሲነሳ በተዋረድ ላሉ የጤና ድርጅቶችና ለመስተዳድር አካላት በየጊዜው /ወዲያውኑ/ ሪፖርት ማድረግ፣

**ቁንጫ**

ቁንጫ እንቁላሏን የምትጥለው መሬት ላይ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ የምትገኘው ንፅሕናው ባልተጠበቀ አቧራ ያለው ወለልና ሰው ለቆ በሰነበተበት ባዶ ቤት ውስጥ ወይም ንፅሕናቸው ያልተጠበቀ የቤት እንስሳት /ድመትና ውሻ/ በሚገኙበት አካባቢ ነው፡፡ ምግብ የሚያገኙት የሰዎችንና የእንስሳትን ደም በመምጠጥ ነው፡፡

**የሚያመጣው የጤና ችግሮች፡-**

- ❖ ተስቦ /ኘሌግ/
- ❖ እንቅልፍና እረፍት ማሳጣት

**ማስተላለፊያ መንገድ**

- ❖ ተስቦ /ኘሌግ/ በቁንጫ ውስጥ በሚገኝ ረቂቅ ተዋህስያን አማካይነት ይተላለፋል
- ❖ ይህ በሽታ በመሰረቱ የአይጥ በሽታ ሲሆን ቁንጫ በኘሌግ /ተስቦ/ የተያዘች አይጥ ከነከሰች በኂላ ወደ ጤናማ አይጥና ሰው በሽታውን ታስተላልፋለች፡፡

**መከላከያ ዘዴዎች፣**

- ❖ የቤት ወለልን ዘወትር ዉሃ በማርከፍከፍ መጥረግ እና በንጽህና መያዝ፣
- ❖ የመኝታ ልብሶችን፣ አልጋ ፊራሽ ወይንም ምንጣፍ በየጊዜዉ በፀሃይ ላይ ማዉጣትና ማናፈስ
- ❖ በተገቢ ቦታ የዉሻ ቤት በመስራት እንዲሁም ዉሻም ሆነ ድመት ከሰዉ ጋር እንዳይገናኙ ማድረግ፣ ንጽህናቸዉን መጠበቅ፣
- ❖ የቤቱ መሰረት አይጥን በሚቋቋም ቁሳቁስ መስራት፣ የአይጥ መግቢያ ቀዳዳዎችን መድፈን፣ መራቢያ ቦታዎችን ማጥፋት፣

**ትኂን**

ትኂን ንፅሕናው በአግባቡ ባልተጠበቀ የመኝታፍራሽ፣አልጋ መገጣጠሚያ፣በተሰነጠቀ ግድግዳና ጣሪያ ውስጥ እንቁላላቸውን በመጣል ይራባሉ፡፡

**የሚያመጣው የጤና ችግር**

- ❖ የሰውን ደም መምጠጥ፣
- ❖ ዕረፍትን በማሳጣት ሰውነትን ያደክማል፣

**መከላከያ መንገድ**

- ❖ የተሰነጣጠቀ የቤት ወለል ጣሪያና ግድግዳን ማደስ፣
- ❖ አልጋ፣ ፍራሽ /ምንጣፍ/፣ የሌሊት ልብሶችን ፀሐይ ላይ አውጥቶ ማናፈስ፣
- ❖ የቤት ዕቃዎችን ወንበር፣ ጠረጴዛ ወዘተ በንፅሕና መጠበቅ፣
- ❖ ቤትን በንፅህና መጠበቅ፣

**በራሪ ነፍሳት**

በራሪ ነፍሳት የሚባሉት ትንኞች፣ ዝንቦች፣ በረሮዎች እንደምሳሌነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ በሽታን በማስተላለፍ ይታወቃሉ፡፡

**ዝንብ**

የግቢያችን ንጽህና በሚገባ ካልተጠበቀ ዝንቦች በቀላሉ እንዲራቡ አመቺ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ ዝንብ ከቆሻሻ አካባቢ ተነስታ ወደ ሰዎች መኖሪያ ቤት በመግባት ከሰዎች ጋር በመኖር የሰዉን ጤና የምታዉክ ናት፡፡ ዝንብ መራቢያዋና መኖሪያዋ የከብት አዘባና ፋንድያ የበሰበሰ ቆሻሻ በጥንቃቄ ያልተያዘ ሥጋ፣ የምግብ ትርፍራፊ፣ ዓይነምድርና የሞቱ እንሰሳት ናቸዉ፡፡

**የሚያመጣው የጤና ችግሮች**

- የደም ተቅማጥ
- ወስፋት
- ኮሌራ
- ዓይን ማዝ
- አሜባ ወዘተ ናቸው

**ማስተላለፊያ መንገድ**

- ቆሻሻ ላይ በማረፍ በእግሮቿ ላይ ባሉት ፀጉሮችና በክንፎቿ የበሽታ ረቂቅ ተዋህስያንን ተሸክማ ምግብና መጠጥ ላይ አርፋ በመበከል፣
- ቆሻሻ ከተመገበች በኋላ ምግብ ለማሟሟት ስትል ከሆዷ በምታስወጣው ፈሳሽ አማካኝነት ምግብን በመበከል፣
- ዓይነምድሯን ምግብ ላይ በመውጣት ምግቡን በመበከል፣
- የአይን ማዝ /ትራኮማ/ ከበሽተኛው ሰው በመውሰድ ወደ ጤነኛ ሰው በማስተላለፍ፣

**መከላከያ ዘዴዎች**

- ደረቅንና ፈሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ መሰብሰብ፣ ማቃጠል ወይም መቅበር፣
- መፀዳጃ ቤት አዘጋጅቶ በአግባቡ መጠቀምና በንፅሕና መያዝ፣
- ምግብና መጠጥን በሚገባ ከድኖ ማኖር፣
- የመመገቢያ ዕቃዎችን አፅድቶ በተገቢው ቦታ ሸፍኖ ማኖር፣
- የቤትና የአካባቢን ንፅህና አዘውትሮ መጠበቅ፣
- የግል ንፅህናን በሚገባ መጠበቅ በተለይ የህፃናትን የግል ንፅህና መጠበቅ፣

- የቤት እንስሳትን ከሰው ለይቶ በረት ውስጥ በማሳደርና የበረቱን ፅዳት በተገቢው ሁኔታ በመጠበቅ፣ በኋላ አውጥቶ ለጓሮ አትክልት ማዳበሪያነት መጠቀም፣
- ዝንብንለማጥፋትየዝንብማጥፊያኬሚካልበጥንቃቄመጠቀም

**በረሮ**

ሙቀት በሚበዛባቸውና ጨለማ በሆኑ በምግብ መደርደሪያ ማስቀመጫ፣ በተሰነጣጠቀ ግድግዳ በተለይም በምግብ ማብሰያ ክፍል ወዘተ ቦታዎች ይገኛል፡፡

**የሚያመጣው የጤና ችግር**

- መጥፎ ሽታ
- ተቅማጥ
- የደም ተቅማጥ
- የአንጀት ተስቦ
- ኮሌራ ወዘተ

**ማስተላለፊያ መንገድ**

- በረሮ በማንኛውም ቤትና ህንፃ ሊገኝ የሚችል ነፍሳት ነው፡፡ በጨለማ ጊዜ ምግቡን ለማግኘት በምግብ ማብሰያ ቤት፣ በምግብ ማስቀመጫ፣ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ በፈሳሽ ቆሻሻ መውረጃ ቦይ፣ በመፀዳጃ ቤት የሚገኝ ሲሆን ልዩ ልዩ የበሽታ አምጪ ተዋህስያን በሰውነት ክፍሉ በመሸከም ምግብና መጠጥ በመበከል በሽታ ያስተላልፋል፡፡

**መከላከያ መንገድ**

- አካባቢንና ቤትን በንፅህና መጠበቅ፣
- ምግብን በተገቢው ቦታ ከድኖ ማስቀመጥ፣
- ቆሻሻን በተገቢው ማጠራቀሚያ ዕቃ ከድኖ ማስቀመጥ፣
- ፀረ-ተባይ ኬሚካል በጥንቃቄ መጠቀም፣

**ቆርጣሚዎች**

በሰዉ ጤናና ንብረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ጉዳት በማድረስ የታወቁት አይጥ፣ አይጠመጎጥና ፍልፈል የተባሉ ናቸዉ፡፡ ቆርጣሚዎች በቤት ዉስጥ ዱቄት የበሰሉ ምግቦችንና ጥራጥሬን የሚመገቡ ሲሆን፣ በእርሻ ቦታዎች ደግሞ በሰብልና በሥራሥሮች ላይ ጥፋት በማድረስ ምርትን ይቀንሳሉ፡፡ ምግብ ለመፈለግ በቤት ዉስጥ በመሯሯጥ ፀጥታንና እንቅልፍን ይነሣሉ፡፡ አይጦች ልብስን ይበላሉ፣ ሰዎችን በተለይም ህፃናትን ይነክሳሉ፣ ጎተራዎችን በስተዉ የተመረተ እህል ያፋስሳሉ፣ ይበላሉ፡፡

**የሚያመጡት የጤና ችግር**

- ተስቦ
- ኘሌግ (ቸነፈር)
- ሳልሞኔሎሲስ (የደም ተቅማጥ)
- የአይጥ ንክሻ
- ትኩሳት
- በንክሻ ጉዳት ማድረስና እንቅልፍ መንሳት፣

**ኢኮኖሚያዊ ችግሮች**

- በእርሻ ቦታና በጎተራ ውስጥ ያለውን እህል ያጠፋሉ፣
- የመኖሪያና የተቋሞች ሕንፃ አካባቢን በመቦርቦር ያበላሻሉ፣
- በልብሶች፣ በመፃሕፍትና በሌሎች ቁሳቁሶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላሉ፣

**ማተላለፊያ መንገድ**

- በበሽታው በተለከፉ አይጦች ሽንትና ዓይነ ምድር የተበከለ ምግብና መጠጥን በመመገብ፣
- በበሽታ ተለክፎ የሞተውን አይጥ የተመገበ አሳማ ስጋን በደንብ ሳይቀቀል በመመገብ፣
- በበሽታው የተለከፈው አይጥ ላይ ያሉት ቁንጫዎች ሰውን በሚነክሱበት ጊዜ፣
- በበሽታው የተመረዘ አይጥ ሰውን በሚነክሱበት ጊዜ፣
- ከቆሻሻ አካባቢ በእግራቸው ተሸክመው የመጡትን የበሽታ ጠንቅ በምግብና መመገቢያ ዕቃዎች ላይ ሲያራግፉና ሲበክሉ፡፡

**መከላከያ መንገዶች**

- በቤትና በአካባቢ የሚገኙ ቀዳዳዎችን መድፈን፣
- የሚኖሩበትን ጉድጓድ ለይቶ በማወቅ በጭስና በፈላ ውሃ አፍኖ መግደል፣
- ምግብ እንዳያገኙ ማንኛውንም ምግብ ከድኖ ማስቀመጥና የምግብ ትርፍራፊንም በአግባቡ ማስወገድ፣
- መሸሸጊያና መኖሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮችን ማስወገድ፣
- ማንኛውንም ቆሻሻ ሰብስቦ በጉድጓድ ውስጥ ማቃጠል፣
- ጎተራዎችንና መኖሪያ ቤቶችን ሁሉ ለአይጦች መረማመጃና መሸጋገሪያ በማያመች ሁኔታ መስራት፣
- ወጥመድ መጠቀም፣
- በድመት መጠቀም::

# 4. ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ በሚመለከት የሚከናወኑ ተግባራት

## 4.1. በቤተሰብ ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃ ማሰባሰብ፤

- በቀበሌዉ የሚገኙ የመኖሪያ ቤቶች ኩሽና ቤት እና የእነስሳት ማደሪያ ከመኖሪያ ቤት የለዩና ያልለዩ
- በቂ አየር ሊያስገባ የሚችል መስኮት ያላቸውና የሌላቸው ቤቶች
- ቤታቸውን በአዲስ ሊቀይሩም ሆነ ሊያሻሽሉ ያቀዱ ቤተሰቦች
- በአካባቢው የሚገኙ ተባዮች በራሪና ተናዳፊ ነፍሳትና ቆርጣሚዎች በቀላሉ የሚራቡበት ቦታ
- በአካባቢው ለተባይ፣ ነፍሳት/በራሪና ተናዳፊ/ ፣ቆርጣሚ እንስሳት ለመከላከል ህብረተሰቡ የሚጠቀምበት ዘዴ

## 4.2. ህብረተሰቡን ያሳተፈ የሥራ እቅድ ማውጣት

- ቅድመ ጥናቱን መሠረት ያደረገና የህብረተሰቡን ሙሉ ተሳትፎ ያካተተ የሥራ እቅድ ማውጣት

- በእቅድ ዝግጅቱ ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማሳተፍ። ለምሳሌ የቀበሌው ግብርና ልማት ተጠሪ የቀበሌ ኮማንድ ፖስት/ስትሪነግ ኮሚቴ አባላትና እንዲሁም የልማት ቡድን መሪዎች ።

- እንደ አስፈላጊነቱ የሳምንት፣ የወር፣ የሩብ ዓመት የ6 ወርና የዓመት የሥራ እቅድ ማውጣት፣

## 4.3 ከ1 ለ5 ትስስር እና የሴቶች ልማት ቡድን ጋራ መስራት

- የመኖርያ ቤት አሰራርና አያያዝ ክፍተት ያለባቸው ቤተሰቦች በመለየት ከ1ለ5 ትስስር መሪዎች ጋር በመወያየት ችግሮችን ለመፍታት በጋራ ማቀድ፣
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎችን የመኖርያ ቤት አሰራርና አያያዝ ዙሪያ ማሰልጠን
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን ሴቶችና ቤተሰቦቻቸው ስለ መኖርያ ቤት አሰራርና አያያዝ እንዲያስተምሩ ማድረግ፣
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን ቤተሰቦች የመኖርያ ቤት አሰራርና አያያዝ እንዲያስተምሩ፣ ተሞክሮአቸው እንዲያጋሩና እንዲከታተሉ ማስቻል፣
- የ1ለ 5 እና የልማት ቡድን መሪዎችን እንደአስፈላጊነቱ በየቤታቸው በመጎብኘት ስራቸውን ማየት፣ ችግሮቻቸውን መፍታትና ማበረታታት፣
- የመኖርያ ቤት አሰራርና ና በራሪ፣ ተናዳፊ ነፍሳት ቁጥጥር ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን ከልማት ቡድኖች ጋር በየጊዜው መገምገም የልምድ ልውውጥ ማድረግና የጋራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ

## 4.4 ለፖኬጁ ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉ ማህበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ከአጋሮች ጋር አብሮ መስራት

- **መስተዳድር-** የወረዳ፣ የቀበሌ እና የልማት ቡድን መሪዎች - ለጤና ተስማሚየሆነመኖሪያቤትአሠራርናአያያዝበተመለከተ ለጤና ኤክስተንሽን ሰራተኛዋ አስተዳደራዊ ድጋፍ በመስጠት፣ ህዝቡ በጋራ በሚያከናዉኑ ስራዎች ላይ እንዲሳተፍ በማስተባበር፣ የተሰጣቸዉን ተግባራት መፈጸም፤

- **ግብርና-** የግብርናልማትሰራተኞችስለ ጤናማ ተስማሚየሆነመኖሪያቤትአሠራርናአያያዝ ዘመናዊ የእህል ጎተራዎች አሰራር፣ ቆጣቢ ምድጃ ሥራ፣ እንስሳት ጤና አጠባበቅና እንክብካቤ፣ የግንባታ ቁሳቁሶች አቅርቦትና ተባዮችና ቆርጣሚዎች ማሰወገድ ስለሚገድ እነዲት እንደሚገባ በቅንጅት አብረው የሰራሉ።

- **ትምህርት-** በግል ንጽህና አጠባበቅ ፓኬጅ ላይ በተገለጸዉ መሰረት ከቤት ንጽህና አያያዝ ጉድለት ምክንያት ከሚከሰቱ በሽታዎች እና ከበሽታ አስተላላፊ ተባዮች (ቅማልና ሙጀሌ ከመሳሰሉት) መከላከል ላይ ትምህርት መስጠት፣ ተመሪዎች ተስማሚ መኖሪያ ቤት ምንነት እንዲያዉቁ ግንዛቤ መፍጠር

- **የሃይማኖት እና ባህላዊ ተቋማት እና ታወቂ ግለሰቦች-** በእምነትስፍራዎችስለተስማሚመኖሪያቤትአሰራርናአያያዝላይትምህርትመስጠት፣ ተከታዮቻቸዉንማስተባበርእናበሞዴልነትማገልገል፣

## 4.5 ህብረተሰቡን በመቀስቀስ በማስተማር፣ በማስተባበር፣ ተሳትፎውን በማሳደግ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ፤

- የተለያዩ ምቹ አጋጣሚዎችን በመለየት በልማት ቡድን እና በቀበሌ የሚደረጉ ስብሰባዎችን፣ በእምነት ተቋማትን፣ ባህላዊ አደረጃጀቶችን እና ትም/ት ቤቶችን … ወዘተ የመሳሰሉት በመጠቀም ለህብረተሰቡ ተከታታይ ትም/ት መስጠት፣
- በቤተሰብ ደረጃ ስለ ጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አስፈላጊነትና አሠራር ሰፊና ቀጣይነት ያለው ትምህርት መስጠት፡፡
- ስለ ተባዮች፣ቆርጣሚ እንስሳትና በራሪና ተናዳፊ ነፍሳት መከላከል በተመለከተ ሰፊና ቀጣይነት ያለው ትምህርት በሁሉም ደረጃዎች እንዲሰጥ ማስተባበር፣ በትምህርት ቤት ላሉ ተማሪዎች ትኩረት ሰጥቶ ማሰተማር የበለጠ ውጤት እነዲመጣ ይረዳል
- የተባዮች፣ ቆርጣሚዎችና በራሪ ነፍሳት መከላከያ መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚዉሉ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች (እንደ አይጥ ወጥመድ፣ …. ወዘተ) ግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በቀበሌዉ የሚገኙ ቤተሰቦች የአይጥ ወጥመድ አቅርቦት እንዲያገኙ በአካባቢ የግብይት ሥርዓት ማመቻቸት፣

## 4.6 አዲስ መኖሪያ ቤቶችን በተሻሻለው የአሰራር ዘዴ አነዲሰሩ ማድረግ

- በየአመቱ ቤታቸውን በአዲስ ሊሰሩ ያቀዱ አባወራዎችን መለየት
- አዲስ ሊሰሩ የተሰቡ መኖሪያ ቤቶች የሚሆን መስፈርቶችን ያመላ ወጥነት ያለው ንድፈሃሳብ ከሚመለከተው አከል ጋር በመሆን በማዘጋጀት በቀበሌ ደረጃ ማሰጸደቅ ና ለሕብረተሰቡ ማስተዋወቅ፡፡
- ከቀበሌአስተዳደርጋርበመነጋገርአዲስቤትየሚሰሩነዋሪዎችየተዘጋጀውንንድፈሀሳብተጠቅመውአነዲሰሩማድርግ
- ሙያዊ ድጋፍ ማድረግና ለተግባራዊነቱ አሰፈላጊውን ክትትል ማድረግ


## 4.7 የነባር መኖሪያ ቤቶችን ማሻሻል

- መሻሻል የሚያስፈልጋቸው መኖሪያ ቤቶች መለየት
- ከቀበሌአመራርጋርበመሆንቤተቸውንለማሻሻልለተለዩትአባ/አማዎራዎችየውይይትመድረክ ማዘጋጀት
- በውይይቱጊዜቤተቸውንያሻሻሉሞዴልቤተሰቦችልምዳቸውንአንዲያከፍሉማድረግ


- በቀላሉቤቱንበመክፈልየአንስሳትመኖሪያእንዴትመለየትእንደሚቻልሰርቶማሳየት
- ሙያዊ ድጋፍ ማድረግና ለተግባራዊነቱ አሰፈላጊውን ክትትል ማድረግ

## የተከፋፈሉአማራጭ የቤትአሰራር

- ይህ ቤት 2 ክፍሎች አሉት አንደኛው የሰዎች መኖሪያ ሌላው የእንስሳት መኖሪያ ነው፡፡
- የእንስሳት መኖሪያ በሩ በውስጥ በኩል እንዲቀለፍ ሆኖ ይሰራል፡፡
- ሰዎች እንስሳትን ካስገቡ በኋላ በአካፋዩ ላይ ያለውን መስኮት በመጠቀም በሩን መዝጋትና መክፈት ይችላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የእንስሳት መኖሪያ በመለየት ያለውን የስረቆት ስጋት ያስወግዳል፡፡



VILLAGE HOUSE SET-UP




### የተከፋፈለቤትየሚሰጠውጥቅም

- ❖ ለቤተሰቡ ልዩ ልዩ አገልግሎት አመቺ ይሆናል፣
- ❖ የምግብመሥሪያና እንዲሁም የምግብ ማዘጋጃ በንጽሕና እንዲጠበቅ ያደርጋል፣
- ❖ የቤተሰቡ የመኝታ ቦታ የተለየና ንጽሕናው የተጠበቀ ይሆናል፣
- ❖ ከከብቶች ጋር አብሮ በመተፋፈግ ሊመጣ ከሚችለው የበሽታ ጠንቅ የቤተሰቡን ጤና ይጠበቃል፣

## 4.8 በሰርቶ ማሳያ በማዘጋጀት ህብረተሰቡ የተሻለ ክህሎት ማስጨበጥ

- ❖ ህብረተሰቡ በቀላሉ አይቶ ስለ ጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራር ሊረዳ በሚችልበት ቦታ ፍቃደኛ የሆኑ ቤተሰቦች በመምረጥና ሰርቶ ማሳያ በመሥራት ሌሎች ቤተሰቦች በራሳቸው እንዲሠሩ ማስቻል፣
- ❖ በቤተሰብ ደረጃ ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት በጋራ ሰርቶ በማሳየት አጐራባች ቤተሰቦች የራሳቸውን መኖሪያ ቤት ሰርተው እንዲጠቀሙ ማስቻል፣
- ❖ በጤናኬላ ፣ በቀበሌ መስተዳድር ጽ/ቤትና በአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከል የተሻሻለ ቤት አሰራር ሰርቶ ማሳያ በማዘጋጀት እነደአስፈላጊነቱ አርሶአደሩን ማሰልጠን፡፡
- ❖ በቀበሌው ውስጥ ገነው እየተገኙ ያሉ ተባይና ቆርጣሚዎችን ለማሰወገድ የሚረዱ በህላዊና ዘመናዊ ተባይና ቆርጣሚዎች ማስወገጃ መንገዶች ከግብርና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ሰርቶ በማሳየት ህብረተሰቡ በስፋት እንዲጠቀሙበት ማድረግ፡፡

## 4.9 ምርጥ ተሞክሮ መለየት፣ መቀመርና ማስፋት

**በቀበሌ ደረጃ**

- በቀበሌዋ ያለውን የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራ ለማሻሻል እንዲረዳት ከጤና ጣቢያ የትስስር አስተባባሪዎች በመመካከር የተሸለ ተሞክሮ ካለው ቀበሌ ልምድ መቅሰም፡-
    - ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ቀበሌ መለየት
    - በተሞክሮው/በልምድ ልውውጡ የሚሳተፉ አባላትን መምረጥ
    - የልምድ ልውውጡን ማካሄድና በቀበሊያቸው እንዴት ማስፋት እንዳለባቸው የሚገልፅ የድርጊት መርሀ-ግብር ማዘጋጀት፣ መተግበር፣

**በልማት ቡድን ደረጃ**

- ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ልማት ቡድኖች መለየት
- ሌሎች ልማት ቡድኖች ተሞክሮውን እንዲጎበኙ መርሀ-ግብር መንደፍ
- የልምድ ልውውጡን ማካሄድና በልማት ቡድናቸው እንዴት ማስፋት እንዳለባቸው የሚገልፅ የድርጊት መርሀ-ግብር እንዲያዘጋጁ ማገዝና ትግበራውን መከታተል፣

## 4.10 የማበረታቻ ዘዴዎች በመጠቀም በጎ ተሞክሮ ያላቸውን ሰዎች ማበረታታት

- በፖኬጁጥሩተሳትፎናእንቅስቃሴላደረጉቤተሰቦችየማነቃቂያስጦታዎችመስጠት፣
- የምስክርወረቀትመስጠት
- የመሥሪያቁሳቁስመስጠት - በአካባቢውበቀላሉየሚገኝ
- በስብሰባላይእንደምሳሌመጥቀስወዘተ

## 4.11 አካባቢያዊና ሕጋዊ ደንቦችን መጠቀም፣

- የአካባቢያዊሕጐችን - ከመንግሥትሕግናደንቦችጋርአጣጥሞመሥራት፣
- የአካባቢውነዋሪበጋራየሚወሰነውመተዳደሪያ ደንብእንዲያወጡማድረግ
- በመንግሥትየሚወጡህጐችንተግባራዊማድረግ፣

## 4.12 የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ማካሄድ፣

- የወጡትን የሥራ እቅዶች፣ግቦች፣ዝርዝር ተግባራትን እንደየቅደም ተከተላቸዉ በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት ወዘተ በመከፋፈል ተግባራዊነታቸውን በኘሮግራም ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
- በወጣው እቅድ መሠረት መፈፀማቸውን ሕብረተሰቡን በማሳተፍ መገምገም፣

- በደረጃ ሶስት ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ የሚከናወኑትን ተግባራት በመለየት አፈጻጸሙን ክትትል በማድረግ ድጋፍ መስጠት፣
- ወራሃዊ ሪፖርቶች ማጠናቀር፣ በየልማት ቡድኖች ለይታ በመተንተንና የስኬት ሁኔታን መገምገም፣ ችግሮችንና ተግዳሮቶችን መለየትና ከነ-መፍተሄዎቻቸዉ ለጎጥና ልማት ቡድኖችና እንዲሁም ለደረጃ-3 ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ግብረ-መልስ እና ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት፣
- ወርሃዊ ሪፖርቶችን ከደረጃ ሶስት በመቀበል እና በማጠናከር ለክላስቴር ጤና ጣቢዎች በመላክ/ማድረስ፣
- የእቅድ አፈጻጸም ስኬቶችን በማጠናቀር፣ በመተንተንና በመተርጎም እንዲሁም በቀበሌ አመራር በታዋቂ ግለሰቦች የተሰጡ ድጋፎችና ተሳትፎዎች በመቀመር በቀበሌ አመራር የጋራ ምክክር ተደርጎበት አመራር ድጋፍና፣ የህዝብ ተሳትፎ እና አጋርነትን የበለጠ በማጠናከር፣

## 5. የጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤቶችን አሰራር ለማስተማርና ለማስረጽ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- አካባቢን ባህላዊ አኗኗር ያገናዘበ መልዕክት ማስተላላፊያ እና ማስተማሪያ ፖስቴር እና ፊልፕ ቻርቶች (ስዕላዊ መግለጫ)
- የቤት ስፋት (ርዝመትን፣ ወርድን እና ቁመትን) ለመለካት የሚረዳ - የሚጠቀለል ሜትር
- ለማስተማሪያነት/ሰርቶ ማሳያነት የሚያገለግል ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት ሥራ የሚዉሉ ቁሳቁሶች- እንጨት፣ሳር፣ ልጥ፣ የአናጺ ስራ መሳሪያዎች፣ … ወዘተ (ሀ/ተሰቡ የሚያመጣቸዉ)
- በስልጠና ወቅት የሚያግዙ ቁሳቁሶች (ማስታወሻ ደብተር፣ ያልተጻፈበት ፊልፕ ቻርት፣ ፐላስቴር፣ ማርኬር፣ እስክሪፕቶ፣ ገመድ፣ በራሪ ጽህፎችና ማንዋሎች፣ የአይጥ ወጥመድ … ወዘተ)
- ሥዕላዊ መግለጫ ያላቸዉ አጋዥ ማንዋሎች እና ማጣቀሻ መመሪያ፣
- ለዳሳሳ ጥናት የሚያግዝ ቅጾችና መጠይቆች
- ለድጋፋዊ ክትትል የሚግዝ ፎርማት/ቅጽ
- የወራዊ፣ የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት ማጠቃለያ ቅጽ/መዝገብ
- የዕቅድ አፈጸጸም መከታተያና መገምገሚያ ቅጽ/መዝገብ
- የቃለጉባኤ መዝገብና ዶሴዎች

## 6. ከጤና ጣቢያ ጋር አብሮ መስራት

የጤና ጣቢያ ባለሞያዎች በተለይም የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ባለሙያ መረጃ አሰባሰብ፣ በቀበሌ ደረጃ ሊወጡ የሚገቡ ህጎችን በማርቀቅና ተሞክሮዎችን በመለየት በመቀመርና በማስፋት አብረው ያቅዳሉ ይሰራሉ። የልማት ቡድን አመራር ስልጠና ጊዜ ሙያዊ እገዛ ያደርጋሉ።

## 7. ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት አሰራርና አያያዝ በአግባቡ በመተግበር የሚጠበቁ ውጤቶች

- ❖ በጤናተስማሚመኖሪያቤትአሰራርናአጠባበቅላይከእቅድማውጣትእስከማስፈፀም ድረስየሕብረተሰቡተሳትፎናልምድይዳብራል፣
- ❖ የልማትሰራዊትአደረጃጀቶችበፓኬጁአስፈፃምበቂመረጃናእውቀት ይኖራቸዋል፣
- ❖ ለፓኬጁሰራተኛድጋፍየሚሰጡተጨማሪየሕብረተሰብክፍሎችይፈጠራሉ፣
- ❖ የቅንጅተዊአሰራርባህልይዳብራል፣
- ❖ በጤናተስማሚመኖሪያቤትአሰራርናአጠባበቅላይየሕብረተሰቡእውቀትናክህሎት ይዳብራል፣
- ❖ ሰዎችከሰዎችእውቀትና ልምድበመቅሰምበራሳቸውአነሳሽነት መኖሪያ ቤታቸዉን ያሻሽላሉ/ ይገነባሉ፤
- ❖ ህብረተሰቡ ለሰው ለእንሰሳትና ለልዩልዩ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ክፍሎችን ሰርቶየ መጠቀም ልምዱ ከፍ ይላል።

## 8. ክትትልና ግምገማ

- ❖ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ የልማት ቡድን መሪዎች በሚያደርጉት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ በመገኘት ክትትል ማድረግ፣
- ❖ በቤት ለቤት በመሄድ ለጤና ተሰማሚ መኖርያ ቤት አሰራርና አያያዝ ስራዎችን ትግበራ መከታተልና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- ❖ ከቀበሌ መስደዳድር ጋር በመሆን ተስማሚ መኖርያ ቤት አሰራርና አያያዝ በሚመለከት ድጋፍና ክትትልና ማድረግ

## 9. የፓኬጁ ጠቋሚዎች /indicators/

- ❖ በመኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ላይ ትምህርት የተሰጣቸ ውሰዎች ብዛት፣
- ❖ የሰውና የአንሰሳት መኖሪያ ቤት የለዩ ቤተሰቦች ብዛት፣
- ❖ የተለያየ ምግብ ማዘጋጃ /ማዕድቤት/ የሠሩቤተሰቦች ብዛት፣
- ❖ ለብርሃንና ለአየር መዘዋወሪያ በቂ መስኮቶች ያበጁ ቤተሰቦች ብዛት፣

- የቤቱ፣ ማዕድቤቱና ቅጥር ግቢው ከተባዮችና ቆርጣሚ እአንሰሳት ነፃ ያደረጉ ቤተሰቦች ብዛት፣
- የቤቱና የማዕድ ቤቱ ወለል፣ ግድግዳ፣ ጣሪያ፣ ወዘተ በንጽህና የጠበቁ ቤተሰቦች ብዛት፣
- ቤቱ በቂ ክፍሎች /ሳለን፣ መኝታ፣ዕቃ/ ያለውን ቤት ለይተዉ የሰሩ ቤተሰቦች ብዛት፣
- የለማዳ እንሰሳት /ውሻ፣ ዶሮ ወዘተ/ የተለየና ንጽህናው የተጠበቀ ቤት የሰሩ ቤተሰቦች ብዛት፣
- ጭስ አልባ ምድጃ በማድ ቤት ሠርተዉ የተጠቀሙ ቤተሰቦች ብዛት፣